በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ። አሜን።

# ትንሣኤ

"ሞተ በፈቃዱ ወተቀብረ በሥምረቱ" ሃይማኖተ አበው ዘአትና. እንዲል። በፈቃዱ ሞቶ በውዱ ተቀብሮ ሦስት ቀን ሦስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በገዛ ሥልጣኑ በዘመነ ማርቆሰ እሑድ በመንፈቀ ሌሊት ተነስቷል። "ወተንሣእኩ በሥልጣነ - ባሕቲትየ" እንዳለ ቅዱስ ቁርሎስ።

ትንሣኤውን በሦስት ቀን ያደረገው ስለምን ነው ቢሉ፡- በማቴ ፲፪ ፤ ፵ "ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊተ ይኖራል" ያለው ቃል ይፈፀም ዘንድ ነው። ምሳሌውም፡- ከርሰ አንበሪ የመቃብር ዮናስ የጌታ ምሳሌ ነው። ትንቢቱን ባወቀ ተናገረ ምሳሌውንም ባወቀ አስመሰለ፤ ፍጻሜው ግን ኃጢአትን በምድር ፣ መርገምን በመስቀል፣ ሞትን በሲኦል፣ ጥፋትን በመቃብር ማጥፋቱን ለማጥየቅ ነው። መቃብሩን ሲጠብቁ የነበሩ አራት ጭፍሮች መግነዝ ፍቱልኝ መቃብር ክፈቱልኝ ሳይል በአካለ ብርሃን ሲነሣ መላእክት ከእግሩ እንደሻሸ ተነጥፈው ሲያመሰግኑት ደንግጠው ሲቻኮሉ ወደ አይሁድ ሔደው ተነሣ አሏቸው። ቢሄዱ መቃብሩን ተከፍቶ አገኙት። ልብሳቸውን እየቀደዱ ይጮኹ ጀመር። አይሁድ እነርሱንም ተኝተን ሳለ ደቀመዛሙርቱ ሰረቁት በሉ አሏቸው።

ሌሎችን ተከትለው ከመቃብሩ ደረሱ። ጌታችንን ወስደወታል እያሉ ሲያለቅሱ መልአኩ "ስለምን ሕያውን ከሙታን መካከል ትፈልጉታላችሁ? ተነሥቷል ከዚህ የለም ከዚህ የለም፤ ይልቁንም ተነስቷል ገሊላ እቀድማችኋለሁ ያላችሁን አስቡ ብላችሁ ለደቀመዛሙርቱ ንገሯቸው" አላቸው። ሄደውም እንደታዘዙት ተናገሩ። ጴጥሮስ እና ዮሐንስ እየሮጡ ሄዱ። መግነዙን እንጂ እርሱን አላገኙም፤ በእውነት ተነስቷል እያሉ ተመለሱ።

ማርያም መግደላዊት ግን የደረሰበትን ሳላውቅ አልሄድም ብላ ቆማ ታለቅስ ነበር። ጌታ ከወደኋላዋ መጥቶ "ምን ሆነሽ ታለቅሻለሽ? ማንንስ ትፈልጊያለሽ" አላት። እርሷም የአትክልት ጠባቂ መስሏት ጌታ ሆይ አንተ ወስደኸው እንደ ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ ፡ እኔም ወስጄ ሽቱ እንድቀባው አለችው። ኢየሱስም "ማርያም" ብሎ ስሟን ሲጠራት ጌታ መሆኑን ተረድታ መምህር ሆይ ብላ እጅ ልትነሳው ቀረበች። ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፣ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ እኔ ወደ አባቴና ወደአባታችሁ ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው አላት። መግደላዊት ማርያምም መጥታ ጌታን እንዳየች ይህንም እንዳላት ለደቀመዛሙርቱ ነገረች።

ለመግደላዊት ማርያም ብርሃነ ትንሣኤውን የገለጠላት አምላካችን በትንሳኤው ለምናምን ክርስቲያኖች ሁሉ ከትንሳኤው ረድኤት በረከት ያሳትፈን። አሜን።

የሰሜን አሜሪካ የሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ ትምህርት ክፍል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።